# ወንጌሉ

## ይህ ነው

ሕይወት የማንኙነት ጉዳይ ነው፡፡

## የወንጌሉ ዋና ዋና ክፍሎች - የሐዋርያት ሥራ 8፥25-40

ቁልፍ አሳብ፤ ስለ ደኅንነት የሚነሡ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች በወንጌሉ ላይግራ ከመጋባት የሚነሡ ናቸው።

የሐዋርያት ሥራ 8፥25-40 የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ መለወጥ ያካፍለናል። ታሪኩ በቀላሉ የማይገኝ አይነት ነው፤ ምክንያቱም የመለወጡ ልምምድ ከእግዚአብሔር አንጻር፣ ከኢትዮጵያዊው አንጻር እና ከፊልጶስ አንጻር ሊታይ ይችላል። ያ የተሟላ ምስሉ ነው።

የምዕራፍ 8፣9 እና 10 ትልቁ ጭብጥ የወንጌሉ በማኅበረሰቡ አጠቃላይ ልዩ ልዩ ክፍሎች ዘንድ መስፋፋቱ ነው። በእያንዳንዱ ምዕራፍ የመለወጥ ታሪክ እናገኛለን። በምዕራፍ 8፥ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በክርስቶስ ወደ ማመን ይመጣል። በዘር ሐረግ ቆጠራ መሠረት ኢትዮጵያውያን የካም ትውልዶች ናቸው (ዘፍጥረት 10፥6 ኩሽ ኢትዮጵያን የሚወክል የብሉይ ኪዳን ቃል ነው)። በምዕራፍ 9፥ የጠርሴሱን ሳውልን መለወጥን እናያለን። ሳውል አይሁዳዊ እና የሴም የዘር ሐረግ ነው፤ (ዘፍጥረት 10፥21)። በምዕራፍ 10፥ የቆርኔሌዎስ (አሕዛብ) መለወጥ ይገኛል። እርሱ የያፌት የዘር ሐረግ ይሆናል፤ (ዘፍጥረት 10፥2-5)።

እነዚህ ቡድኖች ከጥፋት ውሃ በኋላ የተፈጠረውን ማኅበረሰባዊ እና መልከዓ ምድራዊ ክፍፍል ይወክላሉ። ካም፣ ሴም እና ያፌት የኖኅ ልጆች ነበሩ። እግዚአብሔር ከጥፋት ውኃ በኋላ ምድርን እንደገና በሕዝብ ሲሞላ እያንዳንዱ ትውልድ ከእነዚህ ከሦስቱ የአንዱ ነው። ታሪኮቹ ወንጌሉ የግለሰብ ሕይወትን መለወጡን ብቻ ሳይሆን የሚያሳዩት ወንጌሉ የሰው ዘር ቤተሰቦችን አጠቃሎ ሦስቱንም እየደረሰ እንደሆነ ያሳዩናል።

ከታሪኮቹ የመጀመሪያውን እንውሰድ እና የወንጌሉን ሦስት ወሳኝ እሴቶች እንመልከት። እነዚህ እውነታዎች ሁሉን አቀፍ ናቸው።

### 1. ወንጌሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ የኀለበተ ነው።

ይህንን እውነታ ለመገንዘብ ካቃተን ወይም እውነታውን ከተቃወምን ስለ ደኅንነት ለመረዳት ሁል ጊዜ ግራ እንጋባለን። በሰው የኀለበተ ደኅንነትን ሐሰተኛ አስተምህሮ ለመዋጋት የሚያስችሉ 3 መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች አሉ።

- <u>ማንም በሥራው አይድንም፤ (ኤፌሶን 2፥8-9)።</u>

ኤፌሶን 2፥8-9 *"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።"* ይላል።

(ተጨማሪ ጥቅሶች፥ ቲቶ 3፥5፤ 2፥16)

- <u>ማንም በራሱ ሥራ ጽድቅ አይድንም፤ (ፊልጵስዩስ 3፥9)።</u>

ሰዎች መልካም ማንነት ስላላቸው አይደለም የሚድኑት። አንዳንድ ሰዎች ፍጹም ከፉ የሆነ ነገር ፈጽሞ ስላላደረጉ እንደሚድኑ ያምናሉ። ያ ስለ ኃጢአት ምንነት የተሳሳተ መረዳት ነው።

ጥቂት ከረሜላ ከሱቅ ብትሰርቁ ሌባ ተብላችሁ ትፈረጃላችሁ። 100 ከረሜላም ሆነ 1ሚሊዮን ከረሜላ ወይም 1 ብቻ ብትሰርቁ ምንም ለውጥ አያመጣም። የመስረቅ ተግባር ወዲያውኑ ሌባ የሚል ማዕረግን ያሰጣችኋል። በተመሳሳይ መንገድ ኃጢአት ኃጢአተኛ የሚል ማዕረግ እንዲያሰጠን አንድ ጊዜ ወይም 100 ጊዜ ወይም 1 ሚሊዮን ጊዜ ኃጢአት ብንሠራ ምንም ለውጥ አያመጣም።

ሮሜ 3፥23 *“ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤”* ብሎ ይገልጸዋል። ስለ ኃጢአታችን ግዝፈት እና ስለ ኃጢአቶቻችን ብዛት አይደለም ጉዳዩ። ጉዳዩ ስለ ኃጢአት ስለ ራሱ ምንነት ነው። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለይቶናል።

(ተጨማሪ ጥቅሶች፥ ሮሜ 10፥3-4፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥21፤ ማቴዎስ 6፥33፤ ሮሜ 4፥6)

- ማንም በራሱ ውሳኔ አይድንም፤ (ዮሐንስ 15፥16)።

ዮሐንስ 15፥16 *“እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ . . .”*

ዮሐንስ 6፥44 “*የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።”* ዮሐንስ 6፥65 “*ደግሞ፥ ስለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ።”* ደኅንነት ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ የተጸነሰ ነው። (የሐዋ. 13፥48፣ ሮሜ 8፥29፣ ኤፌሶን 1፥3-7) ደግሞም በጸጋው ተግባራዊ ሆኗል (ኤፌ. 2፥8-9፣ 2ኛ ተሰ. 2፥13፣ 2ኛ ጢሞ. 2፥10፣ ቲቶ 1፥1፣ 1ኛ ጴጥ. 1፥1)።

ከተወያየናቸው ጉዳዮች በተለየ የሰው ልጅን ደኅንነትን በግል ጥረት ከማግኘት የሚከለክሉ ሁለት መሻገር የማንችላቸው ቅጥሮች አሉ። <u>በመጀመሪያ</u> እኛ በመንፈስ የሞትን ነንና ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠት የማንችል ነን። ኤፌሶን 2፥1 “*በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤”* በአካል መሞት ማለት አንድ ሰው ለአካላዊ እንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት ሲያቅተው ማለት ነው። መንፈሳዊ ሞት ማለት ለመንፈሳዊ አንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት ሲያቅተው ነው። የሞተ ሰው ምንም ማድረግ አይችልም!

<u>ሁለተኛው</u> መሻገር የማንችለው ቅጥር መሳት ነው። ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን *“ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።”* ብሎ ነግሯቸዋል፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 4፥3-4)። ሰይጣን እና አጋንንቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት እንዳያዩ ለማሳት በንቃት ይሠራሉ።

መንፈስ ቅዱስ የሞተ መንፈስን እንዲያነቃቃ እና የተሳሳተን አእምሮ እንዲያበራ እንፈልጋን። የሞቱ ሰዎች አይንቀሳቀሱም። የተወናበዱ ሰዎችም አያምኑም።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እግዚአብሔር የደኅንነት መንገድን እንዳዘጋጀ ያሳያል። የሞተ መንፈስን ማነቃቃት፣ ለተወናበደ አእምሮ ማብራት እና ወደ አባት ፍቅር መሳብ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው።

በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ በሥራ ላይ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ስልታዊ በሆነ ስፍራ ላይ ወስዶ አስቀመጠው። ቁጥር 26 *“የጌታም መልአክ ፊልጶስን፥ ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው።”* ይላል። *(ይሄ የበረሃ መንገድ ነው።)* ቁጥር 29 ደግሞ “*መንፈስም ፊልጶስን፥ ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው።”* እንዳለው ይነግረናል። ወደ ጃንደረባውን ደኅንነት የመሩት ቅድመ ሁኔታዎች በተለየ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ የተመቻቹ ነበሩ።

መንፈስ ቅዱስ የሰውየውን ልብ በጥያቄዎች እንደሞላም ልትሞግቱ ትችላላችሁ። መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ከትክክለኛ መልሶች ጋር አዘጋጅቶት ነበር። እናም መንፈሱ ጃንደረባውን ወደ ደኅንነት ጠራው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከፊታችን እንዲቀድም፣ መንገዱን እንዲያዘጋጅልን፣ የሰውን ልብ ለደኅንነት እንዲያዘጋጅልን፣ ሙት መንፈስን እንዲያነቃቃልን፣ መወናበድን እንዲስወግድልን፣ እውነትን እንዲሞላልን እና ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለ ግንኙነት እንዲጠራልን ያስፈልገናል።

ከእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ተለይቶ ደኅንነት የለም።

## 2. ወንጌሉ በእግዚአብሔር ቃል እውነቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ለደኅንነት ወሳኝ/እጅግ አስፈላጊ ነው።

- ሮሜ 10፥17፥ *"እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።"*
- ዮሐንስ 5፥24፥ *"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ..."*
- ኤፌሶን 1፥13፥ *"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤"*
- 1ኛ ጴጥሮስ 1፥23፥ *"ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።"*

መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ሥራ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ይገልጣል።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ጃንደረባው ኢሳይያስ 53ን እያነበበ ነበር። ምንባቡ ስለ የእግዚአብሔር በግ የሚናገር ነበር፤ ነገር ግን ጃንደረባው አልተረዳውም ነበር። ፊልጶስ *"የምታነበውን ታስተውለዋለህን?"* ብሎ ጠየቀ። ሰውየውም *"የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?* ብሎ መለሰ። ፊልጶስን እንዲወጣ እና አብሮት እንዲቀመጥ ጋበዘው። ፊልጶስ ሰውየው ከነበረበት ጀምሮ ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና ምን እንዳደረገ እያብራራ ቅዱሳት መጻሕፍትን አሳየው።

ፊልጶስ ክርስቶስ በዮሐንስ 3 ያደረገውን፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 9 ጳውሎስ ያደረገውን፣ አጵሎስ በሐዋርያት ሥራ 18 ያደረገውን፣ እስጢፋኖስ በሐዋርያት ሥራ 7 ያደረገውን አደረገ። እዚህ የተጠቀሱት ሁሉም ሰዎችን ባሉበት ሁኔታ ለመገናኘት ቅዱስ ቃሉን በሚገባ እና በበቂ ያውቁ ነበር።

የምናውቀው ነገር የወንጌሉን መምሪያ ብቻ ከሆነ ውይይቱ ወደ ሌላ ነገር ሲሄድ ግራ እንጋባለን። የወንጌሉን ሙሉ መልእክት ከተረዳነው ግን ሰዎች ጥያቄዎቻቸው እንዳቀረቡት ልክ ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን።

## 3. ወንጌል በእግዚአብሔር ሰዎች ምስክርነት የሚሰፋፋ ነው።

እግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራውን በሰዎች መሣሪያነት አማካኝነት ሊፈጽም መርጧል፤ (የሐዋ. 2፥4 እና 14፤ 4፥8 እና 31፤ 6፥3-8፤ 7፥55፤ 8፥17፤ 10፥1-48፤ 16፥25-34)። ፊልጶስ በእግዚአብሔር እጅ ያለ መሣሪያ ነበር። እንዲሄድ ሲታዘዝ ሄዷል። ሠረገላውን እንዲገናኝ ሲታዘዝ ተገናኝቷል። ክርስቶስን እንዲያካፍል ዕድል ሲሰጠው ኢየሱስን ሰብኳል። ፊልጶስ ዝግጁ ነበር።

እግዚአብሔር ይህንን የወንጌል መልእክት እንዲያካፍሉ ሕዝቡን ይጠቀማል።

- በሐዋርያት ሥራ ኢየሱስ ተከታዮቹን ምስክሮቹ እንደሚሆኑ ነግሮአቸዋል። ፊልጶስ ለጃንደረባው ምስክር ነበር።
- በሮሜ 10፥14-15 ጳውሎስ *"እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" ብሏል።* ፊልጶስ በእግዚአብሔር ተልኮ የእግዚአብሔርን መልእክት አካፍሎ ነበር።
- በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፥21 ጳውሎስ *"በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፥ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።"* ብሏል። እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ወንጌልን ለማወጅ ይጠቀማል፤ ብሎም እርሱ የሚያምኑትን ለማዳን ደስተኛ ነው።

እግዚአብሔር በጥበቡ እርሱ ወንጌሉን በራሱ ሕዝብ አማካኝነት ማሰራጨትን መርጧል። እኛም ይህንን መልእክት ለሰዎች ሁሉ የማካፈል ኃላፊነት ተሰጥቶናል። የእግዚአብሔር የምሥራች ዜና አደራ ተሰጥቶናል እናም ያንን መልእክት እስከ ዓለም ፍጻሜ የመውሰድ ትእዛዝ ተሰጥቶናል።

እግዚአብሔር ይህን አስደናቂ መልእክት በራሱ ሕዝብ አማካኝነት ለማካፈል መርጧል። እርሱ መንፈሱን ሰጥቶናል። እርሱ ቃሉን ሰጥቶናል። እናም እንድንሄድ ተልእኮ ሰጥቶናል።

ወንጌሉ እንዴት እስከ ዓለም ፍጻሜ ይደርሳል? **የእግዚአብሔር መንፈስ - የእግዚአብሔር ቃል - የእግዚአብሔር ሕዝብ።**

## የወንጌል ዝግጅት መርሆዎች - ማርቆስ 4፥1-20

የሰውን ልብ ለወንጌሉ ከማዘጋጀት አንጻር በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ እናተኩራለን። በዚህ ርእስ ላይ ከምርጦቹ አንዱ የሆነው ምንባብ በማርቆስ 4፥1-20 ላይ በክርስቶስ የተነገረው ነው። ያም የአራቱ አፈሮች ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት ሲናገር በጣም የተለመደው ተምሳሌታዊ መግለጫ እርሻ ነው። በዚህ ምሳሌ ኢየሱስ አራት የአፈር ዓይነቶችን ያነሣል። እያንዳንዱ አፈር የሰውን የልብ ሁኔታ እና ለወንጌሉ መልእክት ያለውን አቀባበል ይወክላል። ልክ እንደዚሁም እያንዳንዱ አፈር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚሆነውን ልዩ ልዩ ደረጃ ያለው ዝግጅት ያሳያል። የአፈሩን ዓይነት እና የመንፈስ ቅዱስን ዝግጅት በመረዳት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማግፋት ከመሞከር ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር እንድንተባበር ያስችለናል።

ኢየሱስ፥ *"እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት።"* ብሏል።

ይህ ሰው የዘር ቁናውን ይዞ በመንገድ ዳር እየሄደ ዘሩን ሲበትን በአእምሮአችሁ ሳሉት። ዘሩን እየዘራ እያለ አንዳንዶቹ ዘሮች በመንገዱ ላይ ወደቁ። አንዳንዶቹ በጭንጫ ላይ ይወድቃሉ፤ አንዳንዶቹ በእሾህ ላይ ይወድቃሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በእርግጥ በመልካም መሬት ላይ ይወድቃሉ። ይሄ ምስል ኢየሱስ ስለ ሰው ልብ ሁኔታ እና ለወንጌሉ ዘር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ለማሳየት የተጠቀመበት ምስል ነው።

### ጠንካራ መሬት፤ አንዳንድ ሰዎች ወንጌሉን አይረዱትም (ቁ. 3-4 እና 15)፤

<u>አፈሩ፤</u> (ቁጥር 3-4)፥ *"እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት።"*

<u>የአፈሩ ማብራሪያ፤</u> (ቁጥር 15)፥ *"ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው፥ በሰሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።"*

ይህ ተመሳሳይ ምሳሌ በማቴዎስ 13 እና በሉቃስ 8 ላይ ይገኛል። በማቴ. 13 ማብራሪያ ላይ በዚህ የመጀመሪያ አፈር ላይ የበለጠ ማብራሪያ አለ። ማቴ. 13፥19 ላይ እርሱ *"የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።"* ይላል። ይህ ሰው ወንጌሉን አልተረዳም። ከዝግጅት አንጻር ልባቸው በመንፈስ ቅዱስ አልተዘጋጀም። እነርሱ ለእግዚአብሔር ነገር ደንድነዋል። ጆን ማካርተር ይህን ሰው እንደሚከተለው ይገልጸዋል

> "የማይረዳበት ምክንያት በመልእክቱ ላይ የተጓደለ ነገር ስላለ አይደለም። ነገር ግን በራሱ ልበ ደንዳናነት ነው። እርሱ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ አንገተ ደንዳና ተብሎ የተገለጠው ዓይነት ሰው ነው። ለእግዚአብሔር ነገር ግድ የሌለው እና መንፈሳዊ ለሆነ ነገር ሁሉ ፍጹም ምንም ጆሮ የማይሰጥ ነው። ቃሉ ወደ አእምሮው ወይም ወደ ልቡ በምንም አይነት መንገድ ሰርስሮ አይገባም። ወንጌሉን እንደ ፍጹም ሞኝነት በማሰብ ቅንጣት ታህል ግምት እንኳን አይሰጥም። እርሱ የልቡ አፈር አመድ እና ምንም ጥቅም የማይሰጥ እስኪሆን ድረስ ተወቅጧል፤ ስለሆነም በቋሚነት እና በቀጣይነት መንፈሳዊ ነገርን የሚገልጡ ምንም አይነት ነገሮችን ይቃወማል።"

ይሁንና አንድ ሰው ዛሬ ከወንጌሉ እራሱን ቢለይ እንኳን እኛ ዘሩን ከመዝራት እንድንቦዝን ተፈቅዶልናል ማለት አይደለም።

ለእንደዚህ አይነቱ አፈር እንዴት ምላሽ እንሰጣለን?

- **ጸሎት**
    - የሰውን ልብ ጠንካራ መሬት በእግዚአብሔር ቃል እንዲሰብር ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ። (ሮሜ 10፥14-17)
    - እግዚአብሔር ለእውነቱ ዓይናቸውን እንዲከፍት ጸልዩ (1ኛ ቆሮንቶስ 1፥18፤ የሐዋ. 17፥18-20፤ የሐዋ. 26፥18)
    - እግዚአብሔር ወደ ልብ መነካት እንዲያመጣቸው ጸልዩ። (የሐዋ. 2፥37) በጴንጤቆስጤ ቀን የነበሩት ሰዎች ከክርስቶስ ወንጌል ጋር ፊት ለፊት ሲገናኙ "ልባቸው ተነካ።"

- **ዘር ዝሩ**

የዚህ ሰው ልበ ደንዳናነት በከፊል የብዙ ክርስቲያኖችን ግብዝ የሕይወት ዘይቤ በማየት የመጣ ነው። ዓለም በእግዚአብሔር ኃይል የተለወጠ እና ከዚያ ግንኙነት የተነሣ በዚያ ላይ ተመስርቶ የሚኖር ሰው እየፈለገች ነው። እግዚአብሔር ዕድሉን ሲሰጣችሁ የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወታቸው ላይ አብዝታችሁ ዝሩ። (የቃል ልውውጦች፣ መጻሕፍት፣ ካርዶች፣ ኢሜይሎች፣ ወዘተ፥ ተጠቀሙ)።

- ***ያለቅድመ ሁኔታ ውደዱ***

የሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ ብንወዳቸውም ባንወዳቸውም ካለው ሁኔታ ጋር ፈጽሞ አይገናኝም። ወንጌሉ ስለገባቸው ወደ ጎን እንዳላሉት ማስታወስ የግድ ይገባናል። ወንጌሉን አልተረዱትም። ስለዚህ ይህን ሰው ውደዱት።

## ድንጋያማ አፈር፤ አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስን የመከተልን ዋጋ አያውቁትም። (ቁ. 5-6 እና 16-17)፤

<u>አፈሩ፤</u> (ቁጥር 5-6) *“ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይም ሲወጣ ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ።”*

<u>የአፈሩ ማብራሪያ፤</u> (ቁጥር 16-17) *“እንዲሁም በጭንጫ ላይ የተዘሩት እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፥ ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።”*

**የአፈሩ ባህርይ**፤ ሁለተኛው አፈር የሙግቱ ቀዳሚ ክፍል የሚጀምርበት ነው። ይህ ሰው ቃሉን በደስታ ይቀበላል። ያ ክርስቶስን ተቀብለዋል ማለት አይደለምን? ይህ ሰው ለጥቂት ጊዜ አድጓል። ሕይወት ሳይኖራቸው እንዴት ሊያድጉ ይችላሉ? ይህ ሰው ለጥቂት ጊዜ አድጓል። ሕይወት ካልኖረ ሊታደግ ይችላልን?

ንስሐን ስናስብ የንስሐን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክቶች ልንፈልግ መጠነቀቅ ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስ ዕድገትን የንስሐ ምልክት አድርጎ አይናገርም። <u>መጽሐፍ ቅዱስ ፍሬን ነው የንስሐ ምልክት አድርጎ የሚናገረው።</u>

መጥምቁ ዮሐንስ ምንም ዓይነት የንስሐ ምልክት ሳያሳዩ የጻድቃንን ጥምቀት የፈለጉትን ሃይማኖተኞቹን የሕዝብ ክምችት *“እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤”* ብሎ ገስጿል፤ (ማቴዎስ 3፥8)።

ኢየሱስ በሕይወታቸው ያለውን ፍሬ በማየት በክፉ እና መልካም ሰዎች መካከል መለየት እንደምንችል አስተምሯል። *“ክፉ ፍሬ የሚያደርግ መልካም ዛፍ የለምና፥ እንዲሁም መልካም ፍሬ የሚያደርግ ክፉ ዛፍ የለም። ዛፍ ሁሉ ከፍሬው ይታወቃልና፤ . . .”* (ሉቃስ 6፥43-44)።

በዮሐንስ 15 ላይ ኢየሱስ እርሱ ወይኑ እንደሆነ እና እኛ ቅርንጫፎቹ እንደሆንን እና በእርሱ ያሉ ቅርንጫፎች ሁሉ ፍሬን እንደሚያፈሩ ተናግሯል። ፍሬ በክርስቶስ መሆንን የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነው። ስለዚህ እንደዚህ የመሳሰሉ ምንባባትን ስናጠና ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው “ፍሬን እያየን ነውን?” የሚል ነው።

ይህ የተጠቀሰው ሁለተኛው አፈር ጭንጫ መሬት ነው። ይህ ገለጻ በመሬት ላይ ያሉ ቀላል ድንጋዮችን ወይም ጓሎችን አይደለም የሚጠቅሰው። ገበሬ እርሻውን ሲያርስ ከመዝራቱ በፊት የበዙ ቆሻሻ ነገሮችን ከማሳው ላይ ያስወግዳል። በተቃራኒው እዚህ የተገለጠው ድንጋይ ማረሻው የማይደርሰውን የተጋደመ ዓለት ነው።

የተወሰነ ዝግጅት እንደነበረ ግልጽ ነው። በመንገዱ ላይ የወደቀት ዘሮች (ቁጥር 4) መሬቱ ውስጥ ለመግባት አልቻሉም። በጭንጫ መሬት የወደቁት ዘሮች (በቁጥር 5) መሬቱን ጥሰዋል፤ ግን ላይ ላዩን ብቻ ነው።

ዘሮቹ እዚህ ጥልቀት አልባ አፈር ላይ ሲያርፉ*“በአንዴ በቀሉ . . . ጸሐይ በመጣ ጊዜ ግን ደረቁ፤”* ስሮቹ ውሃ ለማግኘት አልቻሉም። አፈሩም ሕይወትን ለማቆየት በሚያስችል ሁኔታ የለሰለሰ አልነበረም ወይም ከአፈሩ በታች የነበረው ድንጋይ አልተሰበረም።

ይህ ሰው በቁጥር 16-17 በጥልቀት ተገልጿል። *“እንዲሁም በጭንጫ ላይ የተዘሩት እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፥ ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።”*

*ጭንጫማው አፈር ተጋፊ ነው፤ ወንጌሉንም አልተረዳም። ይህ አፈር የሚቀበል ነው፤ ነገር ግን ከወንጌሉ ጋር አብሮ የሚመጣውን ዋጋ አልተረዳም። ይህ ግለሰብ የደኅንነትን ዋጋ ለመረዳት ጠንካራ መሠረት ሳይኖረው ስሜታዊ ውሳኔ (የደስታ ውሳኔ) ያደርጋል።*

*አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኝ ስለዚህ ክፍል እንዲህ አለ፤ "አንዳንድ ጊዜ ወንጌሉን ባልጠለቀ መልኩ መቀበል የደኅንነት በረከቶችን ከፍ አድርጎ በሚይዝ፥ ነገር ግን እንደ ኃጢአትን መናዘዝን፣ ለራስ መሞትን፣ እና ከቀድሞ ሕይወት መለወጥን የመሳሰሉ ዋጋዎቹን በሚደብቅ የቀለለ የወንጌል ስርጭት አማካኝነት ይበረታታል። ሰዎች የክርስቶስን ሙሉ ጥያቄዎች በሚገባ ወደ መጨበጥ ሳይደርሱ ወደ መድረክ ፊት እንዲመጡ፥ እጆቻቸውን እንዲያነሱና ቃል እንዲገቡ ወይም ካርድ ላይ እንዲፈርሙ ሲጠየቁ፤ መልእክቱን ከመስማታቸው በፊት ከነበሩበት ርቀት የበለጠ ከክርስቶስ ለመራቅ ትልቅ አደጋ ውስጥ ይገባሉ። ከእውነተኛው ደኅንነት በሐሰተኛ መሸፈኛ ተሸፍነው የተከለሉ ይሆናሉ።"*

*መንፈስ ቅዱስ አሁንም አፈሩን እያዘጋጀ ነው። እንደሚገባ ሙሉ በሙሉ ለመዘጋጀት በመጠበቅ ፋንታ ይህ ሰው ክርስቶስን የመከተልን ዋጋ ሳይረዳ ስሜታዊ ውሳኔ ያደርጋል።*

*"ጭንጫ ልብ" ያለው ሰው ምን ይመስላል? ይህ ሰው የዳነ ወይም የተለወጠ ይመስላል፤ ግን መለወጡ ስሜታዊ መለወጥ ነው። ምናልባት በፍጥነት እራሳቸውን በእግዚአብሔር ነገሮች (ማለትም ቤተ ክርስቲያን በመሄድ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሳተፍ እና በማገልገል) ውስጥ ያስገቡ ይሆናል። ነገር ግን ስደት በመጣ ጊዜ ከክርስቶስ ሕይወት ጋር እራሳቸውን ለማያያዝ ብቃቱ የላቸውም እናም ወድቀው ይጠፋሉ።*

*<u>ለዚህ የአፈር አይነት እንዴት ምላሽ እንሰጣለን?</u>*

- ***ልክ እንደ የመጀመሪያው አፈር ያለ ቅደም ተከተል ተከተሉ።***
- ***ጉጉትን አስተውሉ፤ ነገር ግን የሚያስከፍለውን ዋጋ በሚገባ አስረዱ።***
- ***እንዲህ ያሉት ሰዎች የሚኖሯቸውን ማንኛውም ጥያቄ እየመለሳችሁ አብራችሁ ጊዜ አሳልፉ።***

## እሾሃማ አፈር፤ አንዳንድ ሰዎች ዓለምን ከእግዚአብሔር የበለጠ ይፈልጋሉ (ቁ. 7 እና 18-19)፤

*<u>አፈሩ፤</u> (ቁጥር 7) "ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው፥ ፍሬም አልሰጠም።"*

*<u>የአፈሩ ማብራሪያ፤</u> (ቁጥር 18-19)፥ "በእሾህም የተዘሩት ሌሎች ናቸው፥ ቃሉን የሰሙት እነዚህ ናቸው፥ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥ የማያፈራም ይሆናል።"*

*ዋናው ሊተኮርበት የተገባው ነጥብ የፍሬ ጉዳይ ወይም የሰብል አጥረት ነው። የንስሐ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክት ዕድገት አይደለም፤ ፍሬ ነው። (ተጨማሪ ማጣቀሻ፥ ማቴዎስ 3፣7፣13፤ ዮሐንስ 15፤ ሮሜ 7፤ ገላትያ 5፤ ኤፌሶን 5፤ ቆላስይስ 1)።*

*ሁለተኛው የሚተኮርበት ነጥብ የአፈር ዝግጅት እያደገ የመሄድ ባህርይ ነው። የመጀመሪያው አፈር ፍጹም ደረቅ እና ወደ ውስጥ ሊዘለቅ የማይችል ነው። ሁለተኛው አፈር ከላዩ ክፍት ነው ነገር ግን እስከታችኛው ክፍል ድረስ ለመውረድ በበቂ ሁኔታ ጥልቅ አይደለም። ሦስተኛው አፈር ከእድገት አንጻር በበቂ ሁኔታ አድጓል። ያንን የምናውቀው ሁሉም ነገሩ ስለሚያድግ ነው። አረሙ ወይም እሾሁ እያደገ ነው። የቃሉ ዘርም እያደገ ነው። አረሙ ወይም እሾሁ መልካሙን ዘር እስኪንቁ ድረስ በበቂ ሁኔታ አድገዋል።*

*ለዚህ ሰው እግዚአብሔር ከሌሎች ብዙ ፍላጎቶቹ መካከል አንዱ ነው። እነዚህ ፍላጎቶችም በእግዚአብሔር አልተወገዱም፤ ነገር ግን በእርሱ በራሱም አልተማረኩም። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን በሕይወታቸው እንደገባ እንደ አንድ ታላቅ ጭማሪ ነው የሚያዩት እንጂ እርሱ ሕይወታቸው አይደለም። ይህንን የምናውቀው በእግዚአብሔር እና በዓለም መካከል ምርጫቸውን እንዲወስኑ ሲጠየቁ ዓለም ስለምታሸንፍ ነው። ይህ ሰው በየዕለቱ የሕይወት ጉዳይ (በብድር፣ በሥራ ቦታ፣ በቤተሰብ ጉዳይ፣ በገቢ፣ በግል ፍላጎቶች፣ መኪኖች ወዘተ፥ . . .) በጣም የተያዘ ስለሆነ በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እውነት ለማረፍ ምንም ጊዜ የለውም። የእግዚአብሔር ነገሮች በዓለም ነገሮች ታንቀዋል።*

*ይህ ሰው በዕድሜ የገፋ የመሆኑ ዕድል ሰፊ ነው። ወጣት"የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት" ግድ አይለውም። ይህ ገለጻ ስለ አንድ የወንጌሉን እውነት ስለሚያውቅ ነገር ግን ከክርስቶስ ሌላ የሆኑ ነገሮችን መፈለግ የመረጠ ሰው ነው።*

ይህ ሰው በከፊል እግዚአብሔርን ይፈልጋል፤ ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ ዓለምን የሚፈልግ ነው። ይህ ሰው መንፈሳዊ ነው ግን የጠፋ ነው። እነዚህ ግንኙነት የሌለው ሃይማኖት ነው ያላቸው። የሚነገረው ምልክት ስሜት፣ ተግባር፣ በቤተ ክርስቲያን መገኘት፣ ወይም ስለደኅንነት መጸለይ እንኳን አይደለም። የሚነገረው ምልክት ፍሬ አልባነት ነው።

የእግዚአብሔር ፍሬ በእነርሱ ሕይወት አማካኝነት እያፈራ አይደለም። በእነርሱ ሕይወት ምንም ደስታ የለም። በአስቸጋሪ ጊዜያት ምንም ሰላም የለም። ለሌሎች ሰዎች ምንም ትዕግስት የለም። ከሌሎች ጋርም ምንም አክብሮት የለም። በምልልሳቸው ምንም ትሕትና የለም። ለቅድስና ምንም ጉጉት የለም። የመንፈስ ፍሬ ማሳያ ምንም ነገር የለም።

<u>ለዚህ አይነቱ አፈር እንዴት ነው ምላሽ የምንሰጠው?</u>

- **ይህን ሰው ሁልጊዜ ውደዱት፤ እናም በፈራጅነት ድምጸት አታናግሩት።**
- **ስለ ልብ መነካት እና ግልጽ እንዲሆኑ ጸልዩ።**
- **እግዚአብሔር ከዚህ ሰው ሕይወት ልብን ከፍለው የሚወስዱ ነገሮችን እንዲያስወግድ እና ከመንፈሳዊ ሁኔታቸው እውነታ ጋር ፊት ለፊት እንዲያገናኛቸው ጸልዩ።**
- **በእነርሱ ፊት መንፈሳዊ ምሳሌ መሆናችሁን ቀጥሉ።**

## መልካሙ አፈር፤ አንዳንዶች ወንጌሉን የሚቀበሉ ናቸው፤

<u>አፈሩ፤</u> (ቁጥር 8)፥ *"ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀና ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ፥ አንዱም ሠላሳ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ አፈራ።"*

<u>የአፈሩ ማብራሪያ፤</u> (ቁጥር 20)፥ *"በመልካምም መሬት የተዘሩት ቃሉን ሰምተው የሚቀበሉት አንዱም ሠላሳ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ ፍሬ የሚያፈሩት እነዚህ ናቸው።"*

አራተኛው አፈር ከመንገዱ የራቀ ነው። አስፈላጊው ጥልቀት እንዲኖረው በሚያስችል መልኩ የታረሰ ነው። መልካም ተክሎችን (ከእሾህ ነጻ የሆነ) ለማቆየት የሚያስችል ብቃት ነበረው። ከሁኔታዎቹ ምቹነት የተነሳም፤ "ፍሬ ማፍራት" ችሏል።

ከዚህ አፈር የሚገኘው የምርት መጠን የእውነት አስደናቂ ነው። ኢየሱስ ስለተትረፈረፈ የሰብል ምርት አጭር አስተያየት እየሰጠ ብቻ አልነበረም። ታሪካዊ ማስረጃዎች እንደሚያለክቱት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ወቅት የሰብል ምርት አማካይ ስሌት ከአንድ ስምንት ያህል የሚሆን ነበር። ኢየሱስ እያጠቀሰ ያለው ስሌት ተአምራታዊ ተብሎ ብቻ ነው ሊገለጽ የሚችል ነው። እርሱ ከ1 30፤ ከአንድ 60 እና ከአንድ 100 ምርት ነው የተናገረው። ገለጻው በዮሐንስ 15 ስለ ፍሬ እና ብዙ ፍሬ ካስተማረው ትምህርት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

የእግዚአብሔር ፍሬ በጣም ግልጽ ነው፤ እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች ስለመሆናቸው መጠየቅ አይገባችሁም። የእግዚአብሔርን እጅ በእነርሱ ሁለንተና ላይ ሆኖ ታያላችሁና።

<u>ለዚህ አፈር አይነቱ እንዴት ነው ምንመልሰው?</u>

**ወንጌሉን በግልጽ አካፍሏቸው እና በክርስቶስ ላይ እምነታቸውን በማድረግ እንዴት ኃጢአታቸውን መናዘዝ እንደሚችሉ እንዲረዱ አግዟቸው።**

ወንጌሉ ምንድን ነው?

- እናንተ እና እኔ ከእግዚአብሔር ጋር **ኅብረት** እንድናደርግ ተፈጥረናል፤ (ዘፍጥረት 2-3፤ ዘሌዋውያን 26፥12)።
- ኃጢአታችን ከዚህ **ኅብረት** ለይቶናል፤ (ኢሳይያስ 59፥2፤ ሮሜ 3፥23፣ 6፣23)።
- ይህንን **ኅብረት** ለማስታረቅ በራሳችን ልናደርገው የምንችለው ምንም ነገር የለም፤ (ኤፌሶን 2፥1-9)።
- ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ለመክፈል በመስቀል ላይ ሞተ፤ (ሮሜ 5፥8-10፤ ኤፌሶን 2፥13-16፤ 1ኛ ዮሐንስ 4፥10)።
- ኢየሱስ እኛ ሕይወት ይኖረን ዘንድ ከሙታን ተነሣ፤ (1ኛ ጴጥሮስ 1፥3)
- ኢየሱስ በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ እምነታቸውን በማድረግ ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ የዘላለም ሕይወት (ወይም የዕርቅ **ኅብረትን**) ይሰጣል፤ (ዮሐንስ 3፥16፤ ዮሐንስ 17፥3፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥38፤ ሮሜ 10፥9)።

እነዚህን መረጃዎች በሙሉ አንድ ላይ ስናደርግ፤ አንዳንድ ሰዎች ወንጌሉን እንደማይረዱ እናያለን፣ እንዳንዶች ክርስቶስን የመከተልን ዋጋ አይረዱም፣ አንዳንዶች በዓለም እስረኛ ሆነዋል እና አንዳንዶች ለወንጌሉ መልካም ምላሽ የሚሰጡ ናቸው። ዘሮቹን የሚዘራ በሁሉም ዓይነት አፈሮች ላይ ይዘራል። የሚያጭድ ግን በመልካሙ አፈር ላይ የበለጠ ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

ያ ማለት ሌሎችን ችላ ማለትን ይጠቁማል ማለት አይደለም። ይሄ ከአንድ ሰው ውስጥ የንስሐ ጸሎትን በማስገደድ፣ በመጫን፣ በመደለል ወይም በመጎትጎት ለማግኘት መሞከር እንደማይገባ የሚያስታውስ ነው። የአፈሩን ሁኔታ በመረዳት ለእያንዳንዱ ዓይነት የሰው ልብ ሁኔታ ልንመሰክር እንችላለን።

## ቀላል የወንጌል ገለጻ

የወንጌሉ መልእክት መሠረታዊ ይዘት ምንድን ነው?

- **እናንተ እና እኔ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንድናደርግ ነው የተፈጠርነው።**
  (ዘፍጥረት 2-3፤ ዘሌዋውያን 26፥12)
- **ኃጢአታችን ከዚህ ኅብረት ለይቶናል።**
  (ኢሳይያስ 59፥2፤ ሮሜ 3፥23)
- **ይህንን ግንኙነት ለማስታረቅ በራሳችን ልናደርገው የምንችለው ምንም ነገር የለም።**
  (ኤፌሶን 2፥1-9)
- **ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ለመክፈል በመስቀል ላይ ሞተ።**
  (ሮሜ 5፥8-10፤ ኤፌ. 2፥13-16፤ 1ኛ ዮሐ. 4፥9-10)
- **ኢየሱስ እኛ ሕይወት ይኖረን ዘንድ ከሙታን ተነሣ።**
  (1ኛ ጴጥሮስ 1፥3)
- **ኢየሱስ በእርሱ ላይ እምነታቸውን በማድረግ ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ የዘላለም ሕይወት (ወይም የዕርቅ ኅብረትን) ይሰጣል።**
  (ዮሐ. 3፥16፤ 17፥3፤ ሐዋ. 2፥38፤ ሮሜ 10፥9)

ይህ የመጨረሻ ክፍል የወንጌሉን አራት ክፍሎች ይዟል፤ ቀላል የወንጌል ገለጻ፣ የወንጌሉን መስመር ማበጀት እንድትችሉ የሚያስችል የሚታተም ወረቀት (አባሪ 8ን ይመልከቱ)፤ ሰፊ የወንጌል ገለጻ፣ እና አንድ ገጽ የሰፊው የወንጌል ገለጻ ሊታተም የሚችል እጥርጥር ይዟል፤ (አባሪ 9ን ይመልከቱ)። ግቡ አሳቦቹን ለማጥናት፥ የወንጌሉን ልዩ ልዩ ክፍሎች ለመረዳትና ከዚያም እነዚህን መርሆዎች ወንጌሉን ለሌሎች ስትናገሩ እንድትጠቀሙባቸው ነው።

ወንጌሉን በቀላሉ የወንጌል ገለጻ መሠረት ማካፈል የመከታተያ መገልገያውን በቀና መንገድ ለመሸጋገር ያስችላል። ወንጌሉ ስለኅብረት/ግንኙነት ጉዳይ ነውና እነዚያ የክትትል መገልገያዎቹም በዚያ ግንኙነት ላይ ያተኩራሉ።

በዚህ ገለጻ መሠረት በተደጋጋሚ ወንጌሉን በማካፈል አሳቦቹ በቤተ ክርስቲያናችሁ፣ በጥናት ቡድናችሁ፣ በምታሰለጥኗቸው ወይም ባልዳኑት አእምሮ ዘንድ ይጣበቃሉ። ግቡ ተመሳሳይ እውነትን በተመሳሳይ ቅደም ተከተል በመደጋገም ግራ መጋባትን ለማስወገድ ነው። በጊዜ ሂደት ሰዎች ተመሳሳይ አሳቦችን በተደጋጋሚ ሲሰሙ ወንጌሉን ያውቃሉ።

እነዚህን አሳቦች ማጥናት እና ተጓዳኝ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጋር መተዋወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። እያንዳንዱን ጥቅስ በቃል መያዝ አይኖርባችሁም፤ ነገር ግን ክፍሎቹን በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ብታሰምሩባቸው ይጠቅማል። በዚህ ገጽ የተሰጠውን ይህን ቀላል የወንጌል ገለጻ ቅጂ በኪስ ቦርሳችሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ እና በተንቀሳቃሽ ስልካችሁ ያዙት።

ከዚህ ቀላል ገለጻ ጋር እራሳችሁን ለማስተዋወቅ ሰፊውን የወንጌል ገለጻ አጥኑ። እያንዳንዱ መግለጫ ያንኑ በአጭሩ የተሰጠውን በጥልቀት ወይም በስፋት የሚያብራራ አሳብ ተከትሎት ይመጣል። እነዚህን ክፍሎች እናንተ ማወቃችሁ እና ለምን ለወንጌሉ ወሳኝ እንደሆኑ መረዳታችሁ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ወንጌሉን አካፍላችሁ ከዚያም ያ ሰው በክርስቶስ ላይ እምነቱን ለማድረግ ዝግጁ ካልሆነ ሰፊው የወንጌል ገለጻ ቅጂ (በሚቀጥሉት ሁለት ገጾች የተዘጋጀውን) እንዲኖረው አድርጉ። ያንን ወረቀት በሌላ ጊዜ እንዲያዩትም ጸልዩ። ተጨማሪ ማብራሪያ በጣም ጠቃሚ ነው፤ ደግሞም ለተጨማሪ መገልገያዎች ማግኛ እንዲሆን ድረ ገጹን ይዟል።

ሰፊው የወንጌል ገለጻ

## የሕይወት ዓላማ ምንድን ነው?

ይህ ጥያቄ ለብዙ ክፍለ ዘመናት ተጠይቋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ መልስ ይሰጠናል።

**የሕይወት ዋናው ጉዳይ ግንኙነት ነው።**

---

ከዘፍጥረት መጽሐፍ እስከ ራእይ መጽሐፍ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግንኙነት መልእክት ይናገራል። ይህ መልእክት ወንጌል (ወይም የምሥራች ዜና) ተብሎ ይጠራል። አንድ ሰው መልእክቱን ሲረዳ እና የእግዚአብሔርን የዘላለም ሕይወት ግብዣ ሲቀበል የሕይወትን ዓላማ ብቻ አይደለም የሚያውቀው፤ ሕይወትን እራሷን ያውቋታል።*

* "ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" – ዮሐንስ 14፥6

## እኔና እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ ነው የተፈጠርነው።

ዘፍጥረት 2-3 አዳም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮ እንደነበረ እና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ የሚችልበት ብቃት ተሰጥቶት እንደነበር ይነግረናል። ታሪኩ መነጋገርን፣ አጋርነትን፣ እና በአዳም እና በእግዚአብሔር መካከል የነበረ ግንኙነትን ይገልጻል።

የእግዚአብሔር የኅብረት መሻት በአዳም የተወሰነ ብቻም አልነበረም። ከእስራኤል ጋር የቃል ኪዳን ግንኑነት ውስጥ ገብቷል። *"በመካከላችሁም እሄዳለሁ፥ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፥ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ።"* (ዘሌዋውያን 26፥12) ኢየሱስ ደቀ መዛሙቱን በእርሱ ላይ እንዲጣበቁ በማዘዝ (ዮሐንስ 15፥1-10)፣ ለሚወዱት እራሱን እንደሚገልጥ ቃል በመግባት (ዮሐንስ 14፥21) እና ተከታዮቹን ወዳጆች ብሎ በመጥራት (ዮሐንስ 15፥15) የኅብረት አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት ሰጥቷል። እያንዳንዱ ምንባብ እግዚአብሔር ለኅብረት ያለውን መሻት ያሳያል።

## ኃጢአታችን ከዚህ ግንኙነት ነጥሎናል።

*"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤"* (ሮሜ 3፥23) ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሕግ መጣስ ሲሆን የኃጢአት ቅጣትም አለ። ሮሜ 6፥23 የእግዚአብሔንር ሕግ መጣስ ቅጣት እንዳለው ይነግረናል። "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።" ደመወዝ ላደረግነው ነገር የሚከፈለን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ሁላችንም ሞት ሊከፈለን ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሞት ሲናገር በመጀመሪያ የሚናገረው ስለብመለየት ነው። አካላዊ ሞት ስንሞት መንፈሳችን ከአካላችን ይለያል። በተመሳሳይ መንገድ በኃጢአታችን የተነሣ መንፈሳዊ ሞት ስንሞት መንፈሳችን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ተለያይቷል። "ነገር ግን በደላችሁ (ወይም ኃጢአታችሁ) በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።" (ኢሳይያስ 59፥2)።

## በራሳችን ይህንን ግንኙነት ለማረቅ ምንም ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም።

በርካታ ሰዎች መልካም ሥራዎች ከእግዚአብሔር ጋር ቀና ግንኙነት እንዲኖራቸው እንደሚያስችሉ ያምናሉ። አለመታደል ሆኖ "ለበቂ መልካም ሥራ" መለኪያ ግልጽ ያለ ማመላከቻ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ "አብዛኛውን ጊዜ መልካም ከሆናችሁ እግዚአብሔር የሚቀበላችሁ ትሆናላችሁ።" ወይም "ሦስት መልካም ሥራዎች አንድ መጥፎ ሥራን ያጣፋል።" አይልም። ለመልካምነት ግልጽ ያለ መስፈርት ከሌለ፥ ምን ያህል መልካም በበቂ ሁኔታ መልካም ነው ሊባል የሚችለው?

መጽሐፍ ቅዱስ ችግራችን የመልካምነት ማነስ እንዳልሆነ እንድናይ ያግዘናል፤ ችግራችን የኃጢአት ውጤት ነው። ኃጢአት ሞት እና መወናበድን ስላመጣብን ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነታችንን መቼም ማስታረቅ አንችልም። ኤፌሶን 2፥1 ያለ ክርስቶስ በመተላለፍ እና በኃጢአት የሞትን እንደነበርን ያስተምራል። 2ኛ ቆሮንቶስ 4፥3-4 ያለ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት በዚህ ዓለም አምላክ እውነቱን ለማየት እንደታወርን ይገልጻል። የሞቱ ሰዎች ስለማይንቀሳቀሱ እና የተወናበዱ ሰዎች ስለማያምኑ ከእግዚአብሔ ጋር ለመታረቅ ምንም ማድረግ አንችልም።

## ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ሊከፍል በመስቀል ላይ ሞቷል።

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ሊከፍል በመስቀል ላይ ሞቷል። የእርሱ ዋጋ መክፈል እርቅን የሚቻል፥ የሚገኝ አድርጎታል። "ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤" (ሮሜ 5፥10)።

## ኢየሱስ ሕይወት እንዲኖረን ከሙታን ተነሳ።

የኢየሱስ ሞት የኃጢአታችንን ቅጣት እንደከፈለልን ወደ የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ የሚያመጣን ደግሞ ትንሳኤው ነው። "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤" (1ኛ ጴጥሮስ 1፥3)። የኢየሱስ ሞት የኃጢአት ዕዳችንን ከፈለ፤ የኢየሱስ ትንሳኤ ግንኙነትን እውን አደረገው።

## ኢየሱስ እምነታቸውን በእርሱ ላይ አድርገው ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ የዘለዓለም ሕይወትን (ወይም የዕርቅ ግንኙነትን) ይሰጣል።

ኢየሱስ ስለ ዘላለም ሕይወት ብዙ ጊዜ ተናግሯል። (ዮሐንስ 3፥15-16፤ 4፥14፤ 5፥39፤ 6፥40) ብዙ ሰዎች የዘላለም ሕይወት ስትሞቱ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ እንደሆነ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ያ ኢየሱስ የተናገረው አይደለም። በዮሐንስ 17፥3 ኢየሱስ "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።" ብሏል። የዘለዓለም ሕይወት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የእርቅ ኅብረትን መለማመድ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የዘላለም ሕይወት ኢየሱስ በፈጸመው ነገር ላይ እምነታቸውን አድርገው ከኃጢአታቸው ለሚመለሱ ተሰጥቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ከኃጢአት የመመለስ ተግባርን ንስሐ ብሎ ይገልጸዋል። ያም አንድ ሰው ኃጢአት አልባ ይሆናል ማለቱ አይደለም። ከኃጢአት ሥራ ይልቅ እግዚአብሔርን ይፈልጋል ማለት ነው።

# የዘለዓለም ሕይወትን እንዴት ላገኝ እችላለሁ?

ዮሐንስ 3፥36 "በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤" ብሎ ይነግረናል። አንድ ሰው የዘላለም ሕይወትን ኢየሱስ ባደረገለት ነገር ላይ እምነቱን በማድረግ ይቀበላል። ኢየሱስ ምን አደረገላቸው? ስለ ኃጢአታቸው በመስቀል ላይ ሞተላቸው፤ ሕይወት እንዲኖራቸውም ከሙታን ተነሣ፤ እናም በክርስቶስ ላይ እምነታቸውን በማድረግ ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙ ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል።

ክርስቶስን መከተል መቼም የማያበቃ ጉዞ ነው፤ ነገር ግን በቀላል ጸሎት ሊጀምር ይችላል። ይህ ጸሎት እንዲመራችሁ ተጠቀሙበት። "እግዚአብሔር ሆይ፥ ኃጢአት መሥራቴን አውቃለሁ። ኃጢአቴም ካንተ እንደለየኝ ገብቶኛል። ኢየሱስ ስለ ኃጢአቴ በመስቀል እንደሞተና በሦስተኛው ቀን ከሙታን እንደተነሣ አምናለሁ። እንደገባኝ መጠን ልክም ኢየሱስ ስለኔ ባደረገው በማመን ከኃጢአቴ እመለሳለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን።"

---

ዛሬ በክርስቶስ ላይ እምነታችሁን ካደረጋችሁ፥ ይህንን ውሳኔያችሁን ለሌሎች እንድታካፍሉ እናበረታታችኋለን። ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ጀመራችሁት ስለዚህ አዲስ ግንኙነት ተጨማሪ መገልገያዎችን ለማግኘት የሚከተለው አድራሻ ውስጥ ግቡ፤ www.thisisthegospel.com.

# ወደ ቤተሰቡ እንኳን ደህና መጣችሁ!

ገላትያ 4፥7